# <u>ለታካሚዎች ፣ ለቤተሰቦች እና ለኦንታሪዮ ማህበረሰብ አባላት</u>

እኛም ዶክተሮች (ሐኪሞች) በቶሮንቶ፥ ፔል እና ዮርክ ወላጆች፥ ልጆች እና ጎረቤቶቻችሁ ነን። አፋጣኝ እርምጃ ካልወሰድን በስተቀር፥ ክልል ታካሚዎቻችን እና ማህበረሰቦቻችን ምን እንደቀረባቸው፤ እና እንደገና በዚህ አመት በጋ ምን ሊያጡ እንደሚችሉ ይታየናል። ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ጋር ጊዜ ማሳለፍ፣ ከእረፍት ጉዞ ወደ ቤት መመለስ እና ለእረፍት ወደ ውጪ መጓዝ፥ የበጋ ሥራዎች እና የበጋ ካምፖች፥ ፒካፕ ቅርጫት ኳስ እና በስራ ላይ ካሉ ባልደረቦቻቸው ጋር ዘና ያለ እረፍት፡፡ የቅርብ ዘመድዎን ማየት የሚችሉት በሆስፒታል ውስጥ እና በረጅም ጊዜ እንክብካቤ ውስጥ ብቻ መሆኑ ራሱ ተጨማሪ ህመም ነበር፡፡ የህዝብ ጤና ምክርን ለመከተል የተቻለውን ሁሉ ሲያደርጉ ቆይተዋል፣ ግን ይህ ብቻ በቂ አልነበረም። ስለዚህ ወረርሽኙን መቆጣጠር፥ ህብረተሰቡን በእግሩ እንዲነሳ ማድረግ፥ የጤና አጠባበቅ ስርዓቱን ወደ መደበኛው መመለስ፥ እና ኢኮኖሚው እንደገና እንዲያድግ ለማድረግ ተጨማሪ አስፈላጊ ነገሮች በአስቸኳይ መፈጸም አለባቸው፡፡

የእኛ የጤና አጠባበቅ ስርዓት ይህ ሦስተኛው ማዕበል ወዴት እንደሚሄድ መቋቋም አይችልም፡፡ ይህ የምናየው አዲስ ተለዋዋጭ ቫይረስ በፍጥነት እየተስፋፋ እና ወጣቱን ህዝብ እየመታ ነው ፡፡ የእኛ የአይ.ሲ.ዩ (ICU) አቅም ከዚህ በፊት እንዲህ ተፈትኖ አያውቅም ነበር። ይህንን ከባድ ፈተና ለመቋቋም ድንገተኛ አደጋውን የሚያካሂዱ ቆራጥ የህክምና እና ሌሎች የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች በዚህ አውራጃ ውስጥ ባሉ ሆስፒታሎች ውስጥ ያሉ ከ የCOVID ክፍሎች እና የአይ.ሲ.ዩዎች እስከ መሰበር ድረስ ተወጥረዋል። የCOVID ህመምተኞች ቁጥር አናሳ በሆነባቸው ከተሞች ውስጥ እንኳን የአይ.ሲ.ዩዎች ከሌሎቹ ክፍለ ሀገሮች በሚመጡ ሕመምተኞች እየተሞሉ ናቸው።

እርስዎም እንደደከሙ እና እንደተጨነቁ እናውቃለን። ቀድሞውኑ፣ ብዙዎቻችሁ በበሽታው የመያዝ ፍርሃት የተነሳ ለኮቪድ ፈተናዎች ከመሄድ ተቆጥበዋል፤ በዚህ የተውሳከ ጊዜ የተለመዱ ቀጠሮዎችዎ ተጓጉለዋል፤ ቀዶ ጥገናዎች እና ሙከራዎች ለሁለት እና ለሦስተኛ ጊዜ ተሰርዘዋል። ባሁኑ ወቅት ቀዶ ጥገናዎችን የመሰረዝ አስፈላጊነት እንኳን በየክፍለ ሃገሩ እንደ አንድ አማራጭ መቆጠሩ አንድ ትልቅ ችግር ፈጥሮብናል፡፡ እነዚህም ለካንሰር፥ ለልብ ህመም፤ ዓይነ ስውርነትን ለመከላከል እና ሌሎች ከባድ ከባድ ህመምን ለማስቀረት የሚደረጉ ቀዶ ጥገናዎች ናቸው። ቀዶ ጥገናዎችን ማዘግየት ማለት፥ የካንሰር በሽታን በሰውነት ውስጥ እንዲሰራጭ ጊዜ መስጠት፥ ማየት የተሳናቸው በቶሎ ማየት እንዳይችሉ ማዘግየት፥ መራመድ ያቃታቸው በቶሎ መራመድ እንዳይችሉ፥ አላስፈላጊ ሞትንም ማስቀረት እንዳይቻል ማድረግ ይሆናል። በኮቪድ (COVID) ተውሳከ ብትያዙም ባትያዙም፥ የሁላችሁንም ጤንነት መንከባከብ ስለመቻል ጉዳይ ያሳስበናል፡፡ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ ወጣት ልጅዎ የመኪና አደጋ ቢደርስበት፥ ወይም ልጅዎ ከባድ የአለርጂ ችግር ውስጥ ቢገባ፥ አያትዎ ድንገት ቢወድቁ እና የጎን ስብራት ቢያጋጥማቸው፥ ስትሮክ ካለብዎትም የሚፈልጉትን የእንክብካቤ ደረጃ መስጠት አንችልም ብለን እንጨነቃለን። አስፈላጊውን እንክብካቤ ለመስጠት በሆስፒታሎቻችን ውስጥ በጣም የሰለጠኑ ሰዎች እና አልጋዎች ያስፈልጉናል፤ ለICU አልጋዎቻችን የሚደረጉት የወደፊት ትንበያዎች (ግምቶች) አስከፊ እና ይቅር የማይሉ ናቸው። ያሁኑ ሁኔታ ካልተለወጠ በስተቀር፥ እርስዎን ወይም የሚወዷቸውን ሰዎች የምንንከባከብበት ክፍል አይኖረንም፡፡ ሆስፒታሎችን በተመለከተ፥ ባለፈው አመት በጣሊያን ውስጥ እና ኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ ክሊፖችን ተመልክተው ይሆናል። አንሳሳት፤ ለውጥ ካላደረግን በስተቀር፥ እኛም በቅርቡ የሚያጋጥመን ተመሳሳይ ችግር ነው።

ይህንን የጤና አጠባበቅ ስርዓታችን ውድቀትን ለማስወገድ መንገዶች አሉ፣ ግን አስቸኳይ እርምጃ ይፈልጋሉ።

በጣም በከባድ ሁኔታ ላይ በሚገኙ አንዳንድ የኦንታሪዎ ሥፍራች እንደምንገኝ የሕክምና ባለሞያዎች (ዶክተሮች) **እኛ ከእናንተ የምንጠብቀው፥ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ፤- ለ MPP እና ለጤና ሚኒስትር እንዲሁም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በኮቪድ ብትያዙ ባትያዙም፥ እናንተም በዚህ ተውሳከ በተቀሰቀሰ ምክንያት ስለጤንነታችሁ ጉዳይ የምትጨነቁ መሆናችሁን እና ከዚህ ወረርሺኝ ለመከላከል አስፈላጊውን እርምጃ በአፋጣኝ መውሰድ እንደሚገባቸው ነው።**

ይደውሉ፣ ይጻፉ፣ ጽሑፍ ይላኩ ወይም በትዊተር ይላኩ፤ COVID ያለበትን የሥራ ቦታ ለመጠበቅ ሲባል፥ በኦንታሪዎ ለሚኖሩ ሁሉ ከዚህ የሚከተሉትንም እርምጃዎች መውሰድ እንደሚገባ፤ ክትባቶችን ባስቸኳይ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎችና ሰፈሮች በማስቀመጥ እና ለሕዝብ ግልጽ፥ እና ወጥነት ያለው መረጃዎችን ማስተላለፍ እንደሚገባ ያሳውቁ።

## COVID እየተሰራጨባቸው ያሉ የሥራ ቦታዎችን ይከላከሉ

የ COVID የሥራ ቦታ መስፋፋት አሁንም ዋና ችግር ነው፡፡ መንግሥት አስቀድሞ ፖሊሲዎችን በማስቀመጥ ተግባራዊ ሆኗል። የነርሲንግ ቤቶችን እና የጡረታ ቤቶችን ከ COVID ለመጠበቅ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች በማውጣት በተግባር አውሏል፡፡ እኛም ከዚህ ተምረን፥ በፖሊሲዎች ላይ ተጨማሪ እርምጃዎችን እንጠይቅ፤

⬥ ኩባንያዎች በፋብሪካዎቻቸው ላይ፥ በመጋዘኖች፥ የሸቀጣሸቀጥ መደብሮች እና የግንባታ ቦታዎች ክትባቶችን በትክክል ወደ ሥራ ቦታዎች የሚወስዱበት ላይ የበለጠ የ COVID ምርመራዎችን እንዲጠቀሙ መደገፍ እና ማስቻል፣

⬥ በጣም በተጋለጡ ሥፍራዎች ክትባቶችን በትክክል ለመውሰድ ፍትሃዊ እና ግልጽ ሂደት ይፍጠሩ፤

⬥ የታመሙ ሰዎች ወደ ሥራ በመሄድ የቤት ኪራይ መክፈልን እንደ አንድ አማራጭ እንዳይወስዱት ይከላከሉ።
በመላው ክፍለ ሃገር COVID በቁጥጥር ውስጥ እስኪሆን ድረስ፥ ሰራተኞች ከታመሙ በቤት ውስጥ እንዲቆዩ፤ በCOVID በማገገሚያ ጊዜያቸው ሁሉ ኩባንያዎች እንዲከፍሏቸው ማድረግ፤ COVID ካለው ሰው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያደረጉ ከመሰላቸውም፥ ሥራቸውን እንደሚያጡ ሳይጨነቁ ለሁለት ሳምንታት በቤታቸው በመታገድ እንዲቆዩ ማድረግ።

⬥ ለአነስተኛ፥ መካከለኛ እና ትልልቅ ንግዶች ድጎማ እና / ወይም ማበረታቻ ያድርጉ፤ ለሠራተኞቻቸው ለሚከፍሉትና ስለ ደህነታቸውም እርዳታ ሊፈልጉ ይችላሉና። የግብር ዶላሮችዎ በጥበብ እንዲጠፋ እንደሚፈለጉ እናውቃለን፡፡ ለእኛም አንድ ሰው ICU ውስጥ ለሚያሳልፈው እያንዳንዱ ቀን 3592 ዶላር ወጪ አለብን። ከሠራተኞቻችንም ሲታመሙ ከቤታቸው ተቀምጠው እንዲያገግሙ ለማድረግ የሚደረግ ዝቅተኛው የቀን ክፍያ 114 ዶላር ነው። እነርሱም የኮቪድ ቴስት እየወሰዱ ራሳቸውን እንዲያገለሉ በማድረግ የሥራ ባልደረቦቻቸውን ላይ ተውሳኩን እንዳያዛምቱ እንፈልጋለን።

⬥ ሥራ ላይ መዋል ያለባቸው ሰዎች ሥራቸውን ለመፈፀም የግድ በአካል መገኘት ላለባቸው ብቻ እንደሚፈቀድ ማረጋገጥ። ከቤት ሊሠራ የሚችል ከቤቱ ሆኖ ይሠራ ዘንድ፥ ንግዶች ሁሉንም ሰው መደገፍ ስለሚፈልጉ ጥቅማጥቅሞችን ወይም ቅጣቶችን ይፍጠሩ፤ ይህንንም የሠራተኛ ሚኒስቴር ባልተጠበቁ ጉብኝቶች ያስገድዳቸዋል።

⬥ ልክ ልጆች ትምህርት ቤት ሲማሩ ማድረግ እንዳለባቸው ሁሉ፥ ሁሉም ሠራተኞች በሥራ ላይ ባሉበት ጊዜ ሁሉ፣ በሁሉም የሥራ ቦታዎች ጭምብል እንዲለብሱ፤ ጭምብላቸውን የሚያወልቁትም ማህበራዊ ርቀትን በመጠበቅ ሲበሉ ብቻ እንዲሆን ይደረግ።

አስፈላጊ ንግዶች ክፍት ሆነው መቆየት ካለባቸው የCOVID ስርጭትን ለማስቀረት በሚያስችል ሁኔታ መሆን አለበት። ምንም እንኳን ደህንነትን ለማረጋገጥ በቤት ውስጥ እንደመቆየት የተሻለ ባይኖርም፥ የኦንታሪዮ ሰራተኞችን በሆስፒታል አልጋዎቻቸው ላይ ከምናያቸው ይልቅ በሥራ ቦታዎቻቸው ላይ ቢቆዩ ነው የምንመርጠው።

**<u>ክትባቶችን ለሚገባቸው በትክክለኛው ቦታ ላይ ያድርጉ-</u>**

ከባድ የCOVID በሽታ በክትባት መከላከል ይቻላል፡፡ በዚህ ጊዜ፥ ጤንነታችንን ለማረጋገጥ፥ ክትባቶች በራሳቸው የጤና አጠባበቅ ስርዓታችን እንዳይፈርስ ለመከላከል በቂ አይሆኑም። ግን ኦንታሪያኖችን መከተብ ነው በረጅም ጊዜ ውስጥ ከወረርሽኙ ለመላቀቅ፥ የኦንታሪዮውን ኢኮኖሚ ወደነበረበት ለመመለስ እና በያለበት መዘጋጋቶች ምክንያት የተፈጠሩ

ጭንቀቶችን ማቆም የሚቻለው። ይህ በተቻለ ፍጥነት እንዲካሄድ ለማድረግ፥ በCOVID የመያዝ፥ የማሰራጨት እና የመታመም ከፍተኛ ተጋላጭነት ላላቸው ሰዎች ክትባት ቅድሚያ መስጠት ይገባል፡፡
በአሁኑ ወቅት፥ ይህ እየተፈጸመ አይደለም ያለው።

ሥር የሰደደ የፍትሕ መጓደል ተጋላጭ በሆኑት ሰፈሮች እና ውስጥ እና ሥርዓታዊ ዘረኝነት ባለበት አካባቢ COVID እጅግ የከፋ ጉዳት አስከትሏል። ስለዚህ በተጠቀሱት አካባቢዎች ከፍተኛ ውጊያ ያስፈልገናል፡፡ በፖሊሲዎችም ላይ የሚከተሉት እንዲታከልባቸው እንጠይቃለን።

◆ ሁኔታዎችን በቁጥጥር ለማዋል እስክንችል ድረስ፥ የተገኙትን የክትባት መጠኖች በኦንታሪዮ ሳይንስ አማካሪዎች ጉባኤ በታወቁ ትኩረት በሚገባቸው ሥፍራዎች በብዛት እንዲላኩ።

◆ የክትባት ስርጭቱ እቅድ ለህብረተሰቡ አባላት ግልፅ መሆኑን ማረጋገጥ እና ያንን ማረጋገጥ፥ ቀጠሮዎችንም በቀላል እንዲዳረስ ማድረግ፥ ነው - ይህንን ለማድረግ ብዙ የፈጠራ መንገዶች አሉ፤ የሕክምና ባለሞያዎችም (ዶክተሮች) ይህንን በሥራ ይውል ዘንድ ለመርዳት ይጓጓሉ።

## ለህዝቡ ግልጽና ተከታታይ ወጥነት ያለው መረጃዎችን ያቅርቡ

ደግነቱ፥ በአሁኑ ወቅት፥ ስለ COVID ከአንድ ዓመት በፊት ከምናውቀው በላይ የበለጠ እናውቃለን። ኦንታሪያኖች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ COVIDን በእንዴት አይነት መንገድ እንደሚያስተናግዱ ግልፅ መመሪያዎችን ይፈልጋሉ። ለዚህም፥ የኦንታሪዮ መንግሥት ስለ COVID የቅርብ ጊዜ እውቀታችንን የሚያስተላልፍልን የታመነ ባለስልጣን መሆን አለበት። በፖሊሲዎችም ላይ የሚከተሉት እንዲታከልባቸው እንጠይቃለን።

◆ ስለ AstraZeneca ክትባት ጥቅሞች እና ከሚሰጠው የግል እና የጋር ጥቅም፥ ሊያስከትል የሚችለው ዝቅተኛ የደም መርጋት በአንፃራዊነት ሲታይ የሚኖረው ጉዳት ዝቅተኛ መሆኑን ለህብረተሰቡ የማሳወቅ ዘዴዎችን ማሻሻል ያስፈልጋል።

◆ አሁንም ረዘም ላለ ጊዜ ወደ መደብሮች እና ወደ ሌሎች የቤት ውስጥ ቅንብሮች ውስጥ መግባቱ አሁንም አደገኛ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

◆ ሰዎች ጭምብል ማድረጉን እንዲቀጥሉ፣ በተቻለ መጠን በቤት ውስጥ እንዲቆዩ እና ከቤተሰቦቻቸው ውጭ ካሉ ሰዎች እንዲርቁ ማበረታታት ያስፈልጋል።

◆ አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜ ወይም በጭራሽ ክትባት ላልወሰዱትም ቢሆን፥ ለሁሉም የኦንታሪያኖች ግልፅ፥ ወቅታዊ፥ እና አስተማማኝ መመሪያ መስጠት ያስፈልጋል። በአሁኑ ወቅት ምን በማድረግ እና ምን ባለማድረግ ደህንነትን መጠበቅ እንደሚቻል፤ ይህ ተውሳክ ከጊዜ ወደጊዜ ራሱን እንደሚለዋውጥ፥ ሳይንቲስቶች የበለጠ ስለ ቫይረሱ ሲረዱ፥ ብዙ ሰዎችም ክትባት ሲሰጣቸው፥ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ ሁኔታዎች እንደሚለወጡ ለሕዝቡ ማሳወቅ ይገባል።

ይህ ወቅት ለኦንታሪዮ ህዝብ፥ ለኢኮኖሚው፥ ለህዝቦቹ ጤንነት እንዲሁም የጋራ መጻኢ ወቅቶች ወሳኝ ጊዜ ነው። ማንም ሰው ይህንን አስከፊ ወቅት ብቻውን ሊቋቋመው አይችልም። ስለዚህ እናንተን ከነቤተሰባችሁ እንዲሁም ጠቅላላ ማህበረሰቡ በጤንነት ተጠብቆ፥ ወደየሆስፒታሉ ማዘውተር እንዲቀርለት ለማድረግ ይረዳን ዘንድ የእናንተን የድምጽ ድጋፍ እንፈልጋለን።

ድምጻችሁን ከፍ አድርጉ ለጓደኞችዎ እና ለቤተሰቦችዎም ይንገሩ፣ ይህንን በማህበራዊ አውታረ መረቦች ያጋሩ ወይም በአካባቢዎ በሚገኝ ጋዜጣ ይጻፉ፤ እናም ለ MPP፥ ለጤና ጥበቃ ሚኒስትር እና ለPremier መደወልዎን፥ መጻፍዎን tweet ማድረግዎንም አይርሱ። **በኮቪድ በCOVID ብትያዙ ባትያዙም፥ እናንተም በዚህ ተውሳክ በተቀሰቀሰ ምክንያት**

**ስለጤንነታችሁ ጉዳይ የምትጨነቁ መሆናችሁን፤ እና COVID እየተሰራጨበት ያለውን የሥራ ቦታዎችን መጠበቅ እንዳለባቸው እና ክትባቶች ለተገቢው ሰው ሁሉ በተገቢው ሥፍራ እንዲሰጥ፥ ለህዝቡ ግልጽ እና ተከታታይ ወጥነት ያለው መረጃ እንዲሰጠውም አሳስቡ።**

ፀሐፊ እና ፊርማ